# ዝክረ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድሕን

ከዳንኤል አበራ (danlinet@yahoo.com)

ብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድሕን ቀዌሳ እነሆ በሞት ከተለየን ድፍን አራት አመታት ተቆጠሩ። ቦዳ (አምቦ) የተጀመረ ሕይወት ማንሀተን (ኒው ዮርክ) ተቋጨ። ግብአተ መሬቱም በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል (አዲስ አበባ) ተፈጸመ። ይቺ ፅሁፍ አራተኛ ሙት አመቱን (February 25, 2006) በማሰብ የግጥም ስራዎቹን በግርድፉም ቢሆን በማውሳት እነሆ የፀጋዬ ዝክር ትላለች።

**የእረፍት ዋዜማ፦**

*ፀጋዬ ከማረፉ አራት አመታት ቀደም ብሎም በዶ/ር ኄራን ሠረቀብርሃን* አስተባባሪነት በዋሽንግተን ዲሲ የፀጋዬ ግጥሞች በሲዲ ተቀርፀው ተመርቀዋል።[1] የስንብት ዝግጅት ይሆን። ትንቢት አስቀድሞ ለነገር እንዲሉ።*

*ፀጋዬ ከማረፉ አስራ አምስት ቀን አስቀድሞ የ«አንድምታ» ባልደረባ አናግሮት ነበር። እስኪ ሁለቱን የሎሬት ፀጋዬን ጥኡም ወጎች ላስቀድም።*

*በአፄ ምኒልክ ዘመን እንግሊዞች ቱርካና ሃይቅ አካባቢ ዝሆን ያድኑ ነበርና አንዴ አደናቸውን ተከትለው ሲገሰግሱ ከኢትዮጵያ ኬላ ደርሰው ኖሮ ድንበር አላሳልፍ ካሉ የኬላ ጠባቂዎች ጋር የተኩስ ልውውጥ ይደረግና ከአዳኞቹ አንዱ በዚሁ ምክንያት ይሞታል። እንግሊዞችም አቤቱታ ያሰሙና ነገሩ አባ መላ (ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ) ዘንድ ይደርሳል። እንግሊዞቹ ያለአግባብ ሰው እንደተገደለባቸው አመልክተው የደም ካሳ እንዲሆናቸው ከኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ መሬት እንዲሰጣቸው ነበር የጠየቁት። አባ መላ ነገሩን ያጠኑና ችግር እንደሌለው ለእንግሊዞቹ ይገልጻሉ። ነገሩ ከመፈጸሙ በፊት ግን ይኸ ህግ እናንተ ሃገርም እንደሚሰራበት ማየት ስለምንሻ በሰነድ መልክ ረቂቁ ካለ እስቲ እንየው። እውነት የእንግሊዝ ሰው የዌልስን ሰው ቢገድል እንግሊዝ ከመሬቷ ለዌልስ የምትሰጥ ከሆነ እኛም እንሰጣለን። እሱም የሚሆነው ለተገደለብን የኬላ ጠባቂ ካሳ የሚሆን ከቱርካና ሃይቅ አካባቢ መሬት ከተረከብን ይሆናል ብለው መለሷቸው።*

*ሌላው ደግሞ ሎሬት ፀጋዬ ከ«**ሕይወት ቢራቢሮ**» ግጥሙ መታተም ጋራ ተያይዞ ለአንድምታ ባልደረባ ያወጋው ነው። መጀመሪያ የግጥሟን ቅንጫቢ ነቢይ መኮንን ከተረከው እነሆ!*

---

*ዶ/ር ኄራን ሠረቀ ብርሃን ከታሪክ ባለሙያነቷ በተጨማሪ ለስነ-ጥበብ ባላት ፍቅር፤ ከስነ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር ባላትም ልባዊና ቤተሰባዊ ትስስር በስፋት ትታወቃለች። ብዙዎች እንደሚመሰክሩላትም "እገዛዋን" የሚለው ቃል ያንሳል፤ በጎ ፈቃድዋን፣ ጊዜዋን፣ ገንዘቧን፣ እውቀቷን እና ያላትን ቤተሰባዊ ትስስር ተጠቅማ ሰሎሞን ደሬሳን፤ ገብረ ክርስቶስ ደስታን እና ፀጋዬ ገ/መድሕንን ከ1970ዎቹ ወደኛ ዘመን የስነጥበብ ቤተሰብነት አሸጋግራልናለች። በአንባቢያን ስም በስነጥበብ አፍቃሪያን ስም ለኄራን እጅ እነሳለሁ።

«…ምን አይተሻል ከቁጤማ፣ ምን አይተሻል ከለምለሙ
ቀን አብረሽ አብበሽ ውለሽ፣ ሲመሽ አብረሽ መስለምለሙ?…
አስተምሪኝ ቢራ ቢሮ፣ ሰው ለመባል አለኝታዬ
ቀድሞ የት ነው መነሻዬ
ሲመሽ የት ነው መድረሻዬ…
ሲተረትማ ሲወጋ፣ ከየብልጭታው ውጋጋን
የሰው አራዊት የአእዋፍ፣ ውስብስብ ነገደ-ጉንዳን
ሲነሳ ሲሮጥ ሲደፋ፣ ሲያጋድል ሲያዛባ ሚዛን
በማይመጠን ታላቅ ኃይል፣ በተፈጥሮ ግዙፍ ሥልጣን
ሊፍተለተል ይወለዳል፣ ሳይነቃ ይወድማል ይባላል
ልደቱ ዕድሜና ሞቱ፣ አለማቋረጥ ይጓዛል፤
ይኸ ይሆን አልፋ - ኦሜጋ? ይኸ ይሆን አስቀድሞ ቃል?»

ፀጋዬ እንዲህ አለ፡፡«እሷ ግጥም በጋዜጣ ታትማ በወጣች ማግስት መንግስቱ ለማ ከቢሮዬ መጥቶ ቢራውን እስቲ አምጣው ወይስ ዝም ብለህ ነው ቢራ ቢሮ ያልከው» ብሎ እንደቀለደብኝ ትዝ ይለኛል፡፡ ትንሽ ትከዝ ብሎም «መንግስቱ ምን የመሰለ ደማም ቋንቋ የነበረው ሰው ነበር፡፡ አሁን እኮ ደማም ቋንቋ የሚናገር ሰው ሁሉ ጠፋ»፡፡ አፈሩ ይቅለለውና ሎሬት ፀጋዬ የኛን ትውልድ <<ጫት አመንዣኪ>> ትውልድ ነበር የሚለው፡፡ እንዲህ እንደነሱ ዘመን ባይጎሉም ውድድሩም ቢጠናባቸውም አሁንም እኮ አንቱ የተባሉ ወጣት ደራሲያን መንግስቱዎች ወጣት ገጣሚያን ፀጋዬዎች አሉን፡፡ ጊዜው ሲደርስ እንዘክራቸዋለን፡፡

አምቦ አካባቢ ልዩ ስሟ ቦዳ ከኦሮሞና ከአማራ ወገኖቹ የተወለደው ፀጋዬ ገና በልጅነቱ ነበር ሶስቱ ቋንቋዎች አማርኛ እንግሊዘኛና ኦሮምኛ የተገሩለት፡፡ በኦሮምኛ መፃፍ ብቻ ሳይሆን መግጠምም፤ እንዲሁም በፈረንሳይኛ ይግባባ እንደነበር የግእዝ ትምህርትም እንደነበረው የሕይወት ታሪኩ ያወሳል፡፡[2] በትምሕርት እየጎለመሰ ሲሄድም ደራሲነቱን ገጣሚነቱን እንዲያ ሲልም ፀሃፊ-ተውኔትነቱን በዋነኛነት በጎልማሳነት ዘመኑ ደግሞ ማህበረሰባዊ ሃያሲነት እና የአፍሪካ የሰው ዘር እና የቅብጥ ቋንቋ እና ባህል ጠቢብነትን አክሎበት እስከ እለተ ህልፈቱ ዘልቋል፡፡ በትዳር ሕይወቱም ከወ/ሮ ላቀች ቢተው ጋር ተጋብተው በስድስት ልጆችና የልጅ ልጆች ተባርኳል፡፡ በኩላሊት በሽታ መለከፉ እና አለመዳኑን እንዲያም ሲል በጉብዝናው ወራት ያላሰበውን ስደት በሕክምና ሳቢያ የአብራኩ ክፋይ ልጆቹ ወዳሉበት አሜሪካ አቅንቶ ቢያሰለስለውም፣ እንደተመኘው ሀገሩ ጦቢያ በዓይኑ ላይ እንደዋለለች ህመሙ ጠንቶበት በዚያው በስደት ሀገሩ አሸልቧል፡፡ የማሳረጊያ ግጥሙም ይህንን ተስፋ ቢስነትን አመላካች ይሆን፡፡

የማይነጋ ሕልም ሳልም
የማይድን በሽታ ሳክም
የማያድግ ችግኝ ሳርም
የሰው ሕይወት ስከረክም
እኔ ለኔ ኖሬ አላውቅም[3]

**የእግር እሳት «እባክህ አንድ ነገር ፍጠርና ጥሩኝ። ለአገሬ አፈር አብቁኝ!»፦**

ብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድሕን ከመሞቱ በፊት የጦቢያን ምድር መርገጥ እንደተመኘ ነው አይምሬ ሞት የቀደመው። በአንድ ወዳጁ አይን እንየው ፀጋዬን ።ጋሽ ፀጋዬን አሜሪካ ሄጄ ደውዬ አጣሁት። ሊታከም ሄዷል አሉኝ-ለዳያሌሲሱ። ሳላገኘው በመቅረቴ ትልቅ ፀፀት ይሰማኛል። በስልክ እንኳ አግኝቼ አናግሬው ቢሆን፤ ቢያንስ የመጨረሻው ድምፁ ውስጤ ይቀር ነበር። ምናልባት የኔንም ድምፅ ይዞት ይሄድ ነበር። ትንሽ ስንቅ ቢሆነው። ከጥቂት ወራት በፊት በአንድ የጋራ ወዳጃችን በኩል «እባክህ አንድ ነገር ፍጠርና ጥሩኝ - ላገሬ አፈር አብቁኝ» የሚል መልእክት ሲልክብኝ በዕንባዬ ነው የሰማሁት። በየከርሞ ሰው ቴያትሩ በገጠሬው በአብዬ ዘርፉ ልሣን፤

…ተረት ሆኜ መቅረቴ ነው፣
ለፍሬ ዕድሜዬ ሳትበቃ
ምኞቴ እንደጉም መጥቃ
ተስፋዬ እንደጉድፍ ወድቃ
የወንድሜን ልጆች ጭምር፣
ለርስታቸው ሳላበቃ!…

ያለኝ ይመስለኛል። ስሜቱን የላከልኝ ያህል ውስጤን ጨረሰኝ። ይኸው ዛሬ እጥፍ ሀዘን የሆነ ነገር ሆነ። አንድ ነገር ፈጥረን ሳንጠራው፣ አስከሬኑን ልንቀበል ነው። ፀፀት ነው!

**ቃል ሕይወት፤ ቃል ሚስጥር፤ ቃል ታሪክ፤ ቃል ሃያል ነው፦**

የሕግ ትምህርቱን በአሜሪካ የትያትር ትምሕርቱን በአውሮፓ የተከታተለው ፀጋዬ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዘንድ የሚታወቀው በገጣሚነቱ እና ፀሃፊ-ተውኔትነቱ ሲሆን ዘመን ሲቀያየር ባወጣቸው እንደ እናት አለም ጠኑ፣ ሀሁ፣ በስድስት ወር፣ እና መልክተ ወዛደር ( ከግጥም እሳት ወይ አበባን) በ1960ዎቹ ቴዎድሮስ 1970ዎቹ ሀሁ ወይስ ፐፑ እንዲሁም ጴጥሮስ ያቺን ሰአት በ1980 ዎቹ ለህዝብ በማድረሱ ስመ ገናና ሆኗል። እነዚህን እና ሌሎች ከሰላሳ የማያንሱ ትያትሮች መድረሱ ብቻ ሳይሆን በማዘጋጀትም ጭምር ተሳታፊ ነበር። በነዚህ ትያትሮችም አንቱ የሚባሉ የሃገራችን ምርጥ ተዋንያን ተሳትፈውበታል።

በትያትሮቹም ሆነ በግጥሞቹ በሳልነት በቃላት አጠቃቀሙ ረቂቅነት እጹብነት የሚታወቀው ፀጋዬ ሃያሲያን ተው ቢሉትም በጅ ሳይል የኖረ ነው። በዚህም የተነሳ ይመስላል ተውኔቶቹ ፈታኞች ስለሆኑ ጎምቱ ጎምቱ ተዋንያንን በዋናነት ሲያሳትፍ የነበረው።

ከነዚህም ጎምቱዎች ወጋየሁ ንጋቱ የእናት አለም ጠኑን ጅሉ ሞሮን ሆኖ ሲጫወት የገጠመውን እንዲህ ሲል በምናቡ ይተርከዋል።«ገራፊው ገብረየስ ጅራፉን እንደ መብረቅ እያስጮኸ የጀግናውን የበላይ ዘለቀን ጀርባ በጅራፍ ይተለትላል። እናት አለም ጠኑ ከነኩታራዎቿ ብቅ ስትል ታየች፤ ልጋጋሙ ነዳዩ ባዩ ዱሽ እጁን ታቅፎ መድረኩን የሃዘን ድባብ አጠላበት፤ ተክልዬ አፈሊቁ አቅራራ፤ ሌሎች ገፀ ባህርያት ብቅ ጥልቅ እያሉ ተደራሲያንን

በስሜት አማለሉ።» ሲቀጥልም የቃለ ተውኔቱ አገላለፅ ራሱ ፈታኝ ነው ይለዋል።[4] ወደ ሎሬት ፀጋዬ ዝርዝር ግጥሞች ከመታደማችን በፊት ወጋየሁ ወዳነሳው ጉዳይ ወደ ፀጋዬ የቃላት ሃይል እንዝለቅ። ፀጋዬ የሚጠቀምባቸው ቃላት ታሪክን ተመርኩዞ ከሁለቱ ቋንቋዎች እንዳስፈላጊነቱ ከነባህሉ እያጣቀሰ እየነቀሰ ነው።

ከአብዛኛዎቹ የሃገራችን ደራሲያን በተለየ ሁኔታ ፀጋዬ የቃላትን ሀያልነት የተገነዘበ ይመስለኛል።የጸጋዬ ቃላት ሚስጥር፤ ሰምና ወርቅ ባይሆኑም ተደራቢ ትርጉም አዘል ናቸው። ባጭሩ የፀጋዬን ግጥሞች ቅኔዎች ናቸው ማለቱ ይቀላል።

ቃል ከፍ ሲልም በሰማያዊው «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።…ቃልም ስጋ ሆነ»።[5] ቃል ዝቅ ሲልም በአለማዊው ሰው ዓይንም (በአምሃ አስፋው) እንዲህ ስንኝ ተሰኝቶለታል።

«**ቃል**»
ማን ያውቃል፣
ይለወጥ ይሆናል ቃል፣
ወደሚጨበጥ አካል።
አስማተኞች ሲደግሙ፣
መተታቸውን ሲያሰሙ፣
እቃ ሲፈጥሩ ከምንም፣
ቃላቸውን ወደ ነገር፣
ምኞታቸውን ወደገዘፍ፣
መለወጣቸው ይሆን?
ማን ያውቃል፣
እንደነበር አስቀድሞ፤
ቃል።[6]

በራሱ በፀጋዬ አፍ ግጥምና ቃልን እንዲህ ያስባቸዋል።«ገጣሚው ውስጣዊና ህያዊ ባህርዩን መርጦ፤ አንቅቶ፤ ውበት አክሎ፤ በአስተዋይ ህሊናችን ውስጥ ቁስሉን የመፈወሱን ጥረት ያደርጋል…ቃል ኃይል ነውና። ቃል ውበት ነውና።ቃል እውነት ነውና። ቃል ሕይወት ነውና።»[7]

**የፀጋዬ ግጥሞች፡-**

የፀጋዬ ግጥሞች ልክ እንደ ማንኛውም ግጥም ይዘታቸው የተለያየ ነው። ነቢይ መኮንን ከጠቃቀሳቸው የተወሰኑትን እናያለን። በመጀመሪያ ግን እስኪ የፀጋዬን የእንግሊዘኛ ግጥሞች[8] እንቋደስ።

«**Dreamer**»

A lover love-rejected
With a spirit dejected,
A monk God-forsaken
Whose total faith is shaken,
Are less lost than dreamer
Into whose peace a “question”
Plunged like a knife
And woke him to life,
To search, to find his way
To dodge, to fight his way
Not dream it away!

«**Who is on whose way**?»

I did not know, oh Sir that I stood on your way
It all happened in chance; argument is unfit,
If we fight, others will benefit,
And as this road is also where my future lay,
Destiny forces me to answer you with “Nay”
Pray lose no temper; lest you commit
A risk to result in a regrettable wit,
For, if there be crime, guilty is just the day;
I am also in yours as you are in my shoes
So do let us shift Sir, to either side
However painful it becomes, we should, though
We realize that it isn’t much to lose
That in spite of us the way is wide

And that after all, some day, both of us go.

«**Tears Inevitable**»

Showers of anguish
Rain, do not exhaust
Ocean of revenge
Of the innermost
Voice of the betrayed
Comfort of the lost,
Tears torn itself
Blood of the heart.

«**Nile**»[9]

I am the first Earth Mother of all fertility
I am the Source I am the Nile I am the African I am the beginning
O Arabia, how could you so conveniently have forgotten
While your breath still hungs upon the threads of my springs
O Egypt, you prodigal daughter born from my first love
I am your Queen of the endless fresh waters
Who rested my head upon the arms of Narmer Ka Menes
When we joined in one our Upper and Lower Lands to create you
O Sudan, born out of the bosom of my being
How could you so conveniently count down
In miserable billions of petty cubic yards
The eternal drops of my life giving Nile to You
Beginning long before the earth fell from the eyeball of heaven.
O Nile, that gush out from my breath of life

Upon the throats of the billions of the Earth’s thirsty multitudes,
O World, how could you so conveniently have forgotten
That I, your first fountain, I your ever Ethiopia
I your first life still survive for you?
I rise like the sun from the deepest core of the globe
I am the conqueror of scorching pestilences
I am the Ethiopia that ‘stretch her hands in supplication to God’
I am the mother of the tallest traveler on the longest journey on Earth
...

ለአባይ ቅኔ ያልዘረፈለት ተቀኚ፣ ስንኝ ያልቋጠረለት ገጣሚ፣ ቃላት ያልደረሰለት ደራሲ፣ ያላዜመለት ድምፃዊ፣ ያልተጠቀሰለት ምሳሌ፣ ወዘተ ... የለም። ሲሻገሩት አድንቀውታል። አምላኪዎቹ ሰግደውለታል - ጪዳ ገብረውለታል። በምንጩ ምንነት ተከራክረውበታል - ሁሉም አወድሰውታል።[10] ግና ማን እንደ ፀጋዬ። እንዲያው እንግሊዘኛውን ትተነው የአማርኛ የአባይ ግጥሙን እስኪ እንይለት። ትንግርት ነው የፀጋዬ አባይ።

**«አባይ»**
አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ
የቅድመ - ጠቢባን አዋይ
የኢትዮጵያ ደም የኩሽ እናት
የዓለም ስልጣኔ ምስማክ
ከጣና በር እስከ ካርናክ
በጡትሽ እቅፍ እንዲላክ
ለራህ ለጸሐዩ ግማድ ፧ ለጣህ ለከዋክብት አምላክ
ከጥንተ ፍጡራን ጮራ፣ የመነጨሽ ከኩሽ አብራክ ::
አባይ የምድረ- ኩሽ መኩሪያ
በቅድመ ታሪክሽ ጥርጊያ
ከደም-ቢያ እስከ ኑ-ቢያ
ከሜምፊስ እስከ ሜሮኤ
በስልጣኔሽ ትንሳኤ
ከዴልታሽ እስከ ዴር- ሱልጣን
ከኡመ-ራህ እስከ ኡመ-ዳርማን ፤
አባይ የአቴስ የጡቶች ግት
ለአለም የስልጣኔ እምብርት ፤

ጥቁር አባይ የጥቁር ምንጭ
የካም የስልጣኔ ፍንጭ ፤
አንቺ የምድረ ዓለም ሲሳይ
በረሀውን ጥለሽ ግዳይ
ሰሀራን እንዳከርማ ተልም
ሰንጥቀሽው በወዝሽ ደም፤
በጥበብሽ ስርወ - ፍና
አንቅተሽ ባንቀልባሽ አዝለሽ፣ የቅድመ ታሪክን ዝና
የራምሴስን አበ -ሲምቦል፣ የመነስን ልዕልና
በአልፋ የአልሙጋን ሐውልት፣ የቢያ-ሀንኬን ፍልስፍና
በኮማምቦ የሰባቃን፣ በናፓታም የኤዛና
ፈላኤ የአቴስን ምኩራብ፣ በልቅጾር የአሞንን ዜና
አባይ ታላቅ ቅድመ ተስፋ
የኪነት ጉባኤ አልፋ
ረቂቅ አባይ ያንቺ መገን
ምጥቀትሽ አይተነተን
የእጅ ማስነሻሽ በረከት
ግብርሽ ከአድማሳት ሲከትት
መንጣለያሽ ከእለት እለት
መሻገሪያሽ ካመት - ዓመት
በመስዋዕት ሲወድቅልሽ
በዝማሜ ሲፈስልሽ
በመመለክ በመመስገን
ጽላትሽ ከዘመን ዘመን
በአዝርዕት አበቅቴሽ ሲታጠን
አቤት አባይ ላንቺ መገን፤
አባይ ረቂቅ የጠቢብ ዘንግ
የከዋከብትን ሰልፍ ደርግ
የጨረቃን ጉዞ ፈለግ
አስቀምረሽ በጠቢብ ዘንድ
በፍሳሽሽ ውጣ ውረድ
በሙላትሽ ሚዛን ረገድ
የሰማይን ጥርጊያ መንገድ
የጊዜ መለኪያ ሰዓት፣ ዚነት ባንቺ ተቀምራ
ከቴቢስ እስከ ዳንዳራ
ብስራትሽን እንደ ደመራ
ስልጣኔሽ እንዳበራ
የመጽሀፈ ሙታን ዜና
አድርጎሽ ቅድመ -ገናና
ዛሬ ወራቱ ራቀና

ምድረ -ዓለም ያንቺን አድናቆት
ፈለጉን መሻት ተስኖት
እንዲህ ባንቺ መንከራተት
ታሪክ ወሮታሽ ጠፍቶበት
ትላንት በባዕድ ጩከት
ዛሬም ባላዋቂ ሁከት
ቋንቋ ለቋንቋ ቢራራቅ
የቅድሚያሽ ንድፍ ላይፋቅ
እዚህ ደማም እዚያ ተማም
መባልሽ ብቻ ባይበቃም
የቅርስሽ ጭብጥ ይዞታ
ሆሄታሽ እስካልተፈታ
አባይ ፋናሽ የሕልም ሩቅ
ፈለግሽም ቢሆን ደቂቅ
እንዴት እንዴት ነበር ብለን
ካልደረስንበት ፈልፍለን
የጥንትዋ አባይ እንዴት ትሆን
አባይ -አቢይ አባይ -ግዮን
ከምንጭዋ የጥበብ ሳሎን
ግሪክ ፋርስና ባቢሎን
ጭረው በቀዱበት ሰሞን፤
አባይ የአማልክት አንቀልባ
የቤተ -ጥበባት አምባ
ከኩሽ የቅድመ -አበው ብሂል
ከተራራሽ አናት ቁልልቁል
የሰው ዘር የታሪክ -ፊደል፣ ገና ከጽንሱ ሲረቀቅ
ሊሰይምም የእትብቱን ቆባ፣ ምጥቀቱን ለማንጸባረቅ
ዘለዓለሙን ለማሳወቅ
እስከሜዲተራኒያ፣ ጢስ እሳትሽ ሲፍለቀለቅ
አባይ አቢይ፣ አባይ ግዮን
ለአማልክቶች አምላክ ለአሞን
የኪነት ምንጩ እምትሆን፤
ለአሩስ ርቱእ አክናፋት
ለነዳዮናይሶስ አባት
ከእምብርትሽ የጸሀይ አምላክ ; ተቀስቶ በሰማያት
ያረበበብሽ እንደ እሳት
ጥቁር አባይ የጥቁር ምንጭ
የካም የስልጣኔ ፍንጭ
የቅድመ ታሪክሽ ጥርጊያ
ከደም -ቢያ እስከ ኑ -ቢያ

የኢትዮጲስ ደም የኩሽ እናት
አባይ የጥቁር ዘር ብስራት
የዓለም ስልጣኔ ምስማክ
ከጣና በር እስከ ካርናክ
በጡትሽ እቅፍ እንዲላክ
ለራህ ለጸሀዩ ግማድ፣ ለጣህ ለከዋክብት አምላክ
ከጥንተ -ፍጡራን ጮራ፣ የመነጨሽ ከኩሽ አብራክ
ሰሀራን እንደ ምሁር ተልም
ያለመለምሽ በወዝሽ ደም
የቅድመ -ጠቢባን አዋይ
አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ ።

ሲያሻው በእንግሊዘኛው ሲያሻው በአማርኛ ግጥም ለፀጋዬ ተገርቶለታል እዚያ አምቦ ጠበል ሲጠመቅ የቋንቋ አማልክት ተገልጠውለት ይሆን።

ፀጋዬ በግጥሞቹ ይዘት ማህበረሰብ ነክ ችግሮችን እንዲህ በምናባችን ይዶላቸዋል። «**ይድረስ ለወንድሜ ለማላውቅህ**» አይነተኛ ምሳሌ ነው።

ለሩቅ ገጠሬ ለገባሩ
ለማላውቅህ ለዳር ዱሩ
ከሁመራ ነህ ከመረብ
አኙአክ ነህ ወይስ ገለብ
ማነህ?
አጋው ነህ ወይስ ሺናሻ
ቅማንቴ ነህ ወይ ፈላሻ
ስምህ የሆነብን ግርሻ
ግራ ጎንደር ነህ መተከል
ባላዋቂ የምላስ ቅርስ
የዘር ንፍገት ስትቀበል
ያለአዳህ ስምህ ሲበከል
እምትችል እምትቀበል፤ እማትሞት
እማትነቀል
ማነህ
ቆለኛ ሸክላ ሰሪ ነህ
ያገር እድር ያገለለህ…

ይለናል።

የፀጋዬ ብሶት ፀፀት ለኢትዮጵያውያን ግፉአን ብቻም አይደል አፍሪካዊ ታጋዮችንም ቢሆን ግብግብ ነው የሚልላቸው። «**እንቅልፍ ነው የሚያስወስድህ**» የተሰኘው ግጥሙ ታንዛኒያ ውስጥ ለተገደለው የሞዛምቢኩ ኢ-ቅኝ አገዛዝ ታጋይ ለኤድዋርዶ ሞንድላንድ ሙሾ ነው።[11]

«**እንቅልፍ ነው የሚያስወስድህ**»
«ዝም አልኳቸው ዝም ይበሉኝ
ትቻቸዋለሁ ይተውኝ

አልነካቸውም አይንኩኝ
ብለህ፤ ተገልለህ ርቀህ
እውነት ይተውኛል ብለህ
እንዴት ተስፋ ታደርጋለህ?...
ተስፋ አርገህስ ምን ልትሆን፤ ወይስ ተስፋው ምን ሊሆንህ?
እንቅልፍ እንጂ የሚያስወስድህ።
«አልጠራቸውም አይጥሩኝ
አይንኩኝ ስሜን አያንሱኝ»
ብለህ እንዴት ትመኛለህ እንደማይተውህ ስታውቀው
የተወጋ በቅቶት ቢኛ የወጋ መች እንቅልፍ አለው
የጅምሩን ካልጨረሰው?
...

ፍቅርም ቢሆን ለፀጋዬ ባይተዋር አልነበረም። በ«ወል»[12]አፃፃፍ ዘይቤ ከፃፋቸው መካከልም ሁለቱ፤«**መሸ ደግሞ አምባ ልውጣ**»(1951 ቢሾፍቱ)[13] እና «**ተወኝ**» (1957 ኒውዮርክ)[14] ይገኙበታል።

«**መሸ ደግሞ አምባ ልውጣ**»
አምባ ወጥቼ እኩለ-ሌት፣ ስለት ገብቼ በስሟ
ከርሞ ሰይጣን በሷ አስቶኝ፣ ልገላገል ከሕመሟ
ጠበሏ አፋፍ በጨረቃ፣ ደጋግሜ፣ ማሕሌት ቆሜ
ሆዴ ቃቶት ባር ባር ብሎ፣ እርቃኔን ከሷ ታድሜ
ደጃ ሰላሟን በአራት እግር፣ ተንበርክኬ ተሳልሜ
በሥጋዬ እሚነደውን፣ በጸሎት ላቤ አጣጥሜ
እፎይ ብዬ አመስግኜ፣ ውዳሴዋን ደጋግሜ...
ገና ከደጅዋ እልፍ ሳልል፣ ደሞ ይምጣ የቁም ሕልሜ?
ሌት በጥምቀቷ የነጣው፣ ነጋ፣ ደፈረሰ ደሜ።
ለሷ እንጂ ለኔ አልያዘልኝ፣ አዬ የስለት አታምጣ!
በውጣ ውረድ በጠበል፣ ባሣር ወዜ ቢገረጣ
ልክፍቷ እንደሁ አልለቀቀኝ፣ መሸ ደግሞ አምባ ልውጣ!

«**ተወኝ**»
ላታስታምም አትመመኝ
ላትወስደኝ አታንጠልጥለኝ
ይቅር፣ አንጀቴ ቁረጠኝ
ጋሽዬ፣ አልወድሽም በለኝ
እጅ እጅ አልበል አታባክነኝ
ባክህ፣ ወንድ ነው ቆራጡ፣ እንትፍ እርግፍ አርገህ ተወኝ
አየህ፣ እንዳንተ አባት አለኝ
ሴት በወለድኩ ተዋረድኩ፣ ረከስኩ፣ ቀለልኩ እሚለኝ
እኔም እንዳንተ እህት አለኝ

ስጋሽን ሳይሆን ልብሽን፣ ከፍተሽ ጥለሽ እምትለኝ
እና ተወኝ፣ ባክህ ተወኝ
እንዳንተ እኔም አለኝ እናት
የሴት ቁንጮ እምመስላት
ጎረቤት ፊት እምታፍር፣ እንዲህ ሆነችልሽ ሲሏት!..
እና አልሆንሽም በለኝ
ባክህ አንጀቴን ቁረጠኝ...
ፍቅር እንደሁ የኔ ይበቃል፣ ላንተም ለኔም እኔው ልውደድ
ከዘመድ ግንባር ደብቄ፣ እኔ ብቻዬን ልንደድ
ብቻ፣ ከወጥመድህ ለየኝ
አልችልህም፣ ንቀህ ማረኝ
ካንተም፣ ከስሜም ከቤቴም፣ ያጣሁ ብኩን አታድርገኝ
ባክህ፣ አንጀቴን ቁረጠኝ
ተወኝ፣ ተወኝ፣ ተወኝ።

የፀጋዬ ግጥሞች ፍቅርን ብቻ ሳይሆን የቁጣ ረመጥና መራር ይሆናሉ። «**እንደ መትፋት ያስነውራል**»[15] አይነቶቹ።

«**መትፋት ያስነውራል**»
እፍ አንቺ መብራት ጨልሚ!
እፍ አንቺ መብራት ክሰሚ!
ጥፊ፣ ጨልሚ፣ ውደሚ!...
አለ አሉ ሼክስፒር ቁሱ
መቾም አያልቅበት እሱ...
መድረክ ላይ ኩስ ከሚተፉ
አዎን ሕይወት ራሷ ትጥፉ...
...አዎን መትፋት ያስነውራል
ኪነት የህሊና ጽዳት፣ አስቀድሞ ይጠይቃል
ታዲያን በኛስ መድረክ መቅደስ፣
ለምን አጉል ኩስ ይጣላል?...
ይኸ በመድረክ ላይ መድረቅ
መራቆት እርቃን አፍ መንጠቅ
«ለእንጀራዬ ብዬ» ብሎ፣ በሰበብ ነብስ መሽብለቅ
ስሜት አልባ ሀፍረተ-ቢስ፣
እድፍ ቃል ደርሶ መሰንጠቅ
ለሆድ ብሎ ሐቅን ማነቅ
በጥበብ ስም አጉል ቅሌት፣
መዋረድ ፋንፉር መደለቅ
ህዝብ ፊት በየአዳራሹ፣

ርካሽ ትርዒት ማስገምገሙ
በመጠጥ እየታጠኑ፣ ቃለ-ህሊናን ማጨለሙ
መቼም አትሉት የላችሁ፣
ኪነት ነው አላችሁ ስሙ?...»

የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ባህላዊ እሴትም ቢሆን ከፀጋዬ እይታ የተሰወረ አልነበረም። በ«**የት አባቱ! ሞትም ይሙት**!» የዶርዜ ባህላዊ ሥርአት በሞት ላይ ድል መጎናጸፍ መሆኑን ያበስረናል።[16]

«**የት አባቱ! ሞትም ይሙት**!»[17]
እባካችሁ ዘመዶቼ፣ ስሞት ሞትም አብሮኝ ይሙት
በሳቅ በደስታ ግደሉት
በሃሴት በዕልልታ ውገሩት፤
እባካችሁ ዘመዶቼ፣ ለሞት የልብ ልብ አትስጡት
ናቁት አጥላሉት አውግዙት
በሙሾ ግነን አትበሉት
በሞቴ፣ እንዳታስደስቱት።
እንደ ዶርዜ ወንድሞቼ
በሳቅ ታጅቤ ኮርቼ
ሞቴን በዘፈን ሞልቼ
በዳንኪራ ስበቃና፣ በዘፈን ሆይታ አካትቼ
በሥርጌ ብቀበር ሞቼ
እፀድቅ ነበር ባትረሱ
በእንባ ውሌን ባታፈርሱ።
እባካችሁ ዘመዶቼ፣ በሳቅ ጉዞ ፍታት ፍቱኝ
በሙሾ ዋይታ አታጅሉኝ፤
እናቴም ፊትሽ አይክሰል
በእልልታ ብርሃን ይንበልበል፤
በእረፍቴ እንዳታፈኀርብኝ
በሥርጌ እንዳታለቅሽብኝ።
ገጽሽ በጭንቅ አይወረስ
ልብሽ በኀዘን አይላበስ
በሆድሽ ሞት አይፀነስ
ዕንባ በአይንሽ አይቋጠር
የሞት ቅስሙ እንዲሰበር።
አዎን፣ አደራ፣ አደራችሁ፣ የሙት ውሌን ተቀበሉኝ
ደስታዬን ተካፈሉኝ
ለንስሃ ሞት አይደለም፣ ለፍሥሐ እረፍት አብቁኝ፤
ደስታዬን ተካፈሉኝ
ለንስሃ ሞት አይደለም፣ ለፍሥሐ እረፍት አብቁኝ፤

በዶርዜ እስክስታ አስቀብሩኝ
በእልልታው ጉዞ አሳጅቡኝ
በጦሩ ችቦ አሳጥሩኝ፤
ጭብጨባችሁ በስልቱ ይውረድ
ዛፍ ቅጠሉም አብሮ እስኪረግድ፤
ሀገር ምድሩም ያቅራራ
ሀሴት ነው ይበል፣ ጀቢራ
ሠርጌ ነው፣ ይምታ ዳንኪራ
እንዲህ ስሜት ሲፍለቀለቅ፣ ሲፈነድቅ ሲግል ሃሞት
ቱማታው ሲዋጥ በላቦት
ሆይታ በሆይታ ሲራኮት
ማሳለፊያ መግቢያ ሲያጣ፣ ፍርሃት ገበናው ሲራቆት
መቃረቢያ ፍንጭ ሲያጣ፣ በእልልታ ሲወገር ብሶት...
ብቻ ነው፣ ሞት እራሱ የሚሞት።
እባካችሁ ዘመዶቼ፣ ሞትም አብሮኝ ይሙት!
በእልልታችሁ ግደሉት
በዳንኪራችሁ ዉገሩት
ከአጥንቴ በታች ቅበሩት።

ፀጋዬ ዝነኛ በሆነበት በመልከዓ ምድራዊ ይዘት ግጥሞቹም ይዘከራል። እንደ «**መርካቶ**»፤ «**አምቦ**»፤ «**ድሬ ዳዋ**»፤ «**አንኮበር**»፤ «**አዘቦ**»፤ «**አባይ**» እና «**ሊማሊሞ**» ተጠቃሾች ናቸው።

በነቢይ መኮንን እይታ ፀጋዬ በ«**ሊማሊሞ**» ግጥሙ ልዩ ልዩ እኩያን እየፈጠረ ሊማሊሞን እሱ ባየበት ዐይኑ ሲያሳየን እናገኘዋለን። ሊማ ሊሞ የምድር ኬላ ነው። ሊማሊሞ ለምድር ዘብ የቆመ ነው። ሊማሊሞ ለጠፈሩ ደግሞ ዋልታ ሆኖ የቆመ ነው። ሊማሊሞ የማይበገር የአለት ጣራ ነው። መከታና ጋሻ ነው። ሊማሊሞ በዐይናችን የምናየውን ሰፊ አድማስ ሰብሮአል። ግና ምን ያደርጋል ሥልጣኔ የማይረታው የተፈጥሮ አካል የለም ነው የሚለን ፀጋዬ። በላዩ ላይ መንገድ ወጣበት ነው ያ ግዙፍ አይበገሬ አካል የሚለን ፀጋዬ።

«**ሊማ - ሊሞ**»
የሰማይ የምድሩ ኬላ፣ የየብስ የጠፈሩ ዋልታ
አይበገር የአለት ጣራ፣ አይመከተው መከታ
ሊማ - ሊሞ የቁም እርሙ፣ ሰማይ - አዘል ሊማ - ሊሞ
ከንፉ ከነካስማው ዘሞ
ከጠፈር ውሃ ገድቦ ለየብስ እንደማገር ቆሞ
ተጠማዝዞ ተጠምጥሞ
ከጽንፍ ጽንፍ አረምሞ
ከደባርቅ እስከ አዲ አርቃይ
አለት ከደመና በላይ
አዘንብሎ እንደ ሰማይ

እንደጠፈር ሽቅብ ሲታይ፤
ጉም አጥልቆ እንደቀሚሱ
ፀሐይን እንዳንገት ልብሱ
ተከናንቦ ተሸላልሞ
ተንደላቆ ሊማ- ሊሞ፤
ጨረር ባደመቀው ጭጋግ
ዙሪያ ዘርፉን እንደጎዳግ
በንዳድ ሀሩር ምድጃ
ፍም አንጥፎ እንደ ሥጋጃ፤
ሰማዩን ቁልቁል ዘንጥፎ
በብብቱ ጉም ታቅፎ
የአድማሳቱን ፍንጣቂ፤ ለእግሩ መርገጫ አርከፍክፎ
እንደ ፍካሬ ኢየሱስ ቃል፤ እንደ ሙታን የግዞት ሕግ
ተውተብትቦ ተጥለፍልፎ፤ ተቆላልፎ እንደዛር - ድግ
በምድር በሰማይ ዳር ድንበር፣ በሕዋው አለም ክልል ጥግ
በሲያል ጠፍር መሰላል፤ የብስ ከጠፈር ታድሞ
ጥጉን እንደራእዩ አውታር፤ ከነአክናፉ ቁልቁል ዘሞ
እንደእንጥርጦስ በር አጥር፤ በአለት ናዳ ተረምርሞ
የጉም ክናዱን እንደጣር፤ ወደ ምድር ማኅፀን ቆልሞ
እንደባቢሎን ግንብ አጥር፤ ቋንቋ ለቋንቋ አሳድሞ
አልበገር አልደፈር፤ አልሰበር ያለን ከርሞ
ሊማ-ሊሞ የቁም-እርሙ ጠፈር አዘል ሊማ-ሊሞ
ዛሬ እንደስለት ሃጅ ፈለግ፣ በግብረ-ጉንዳን ተተልሞ
ሰማይ ከምድር ተደላድሎ፤ ተኮትኩቶ ተከርክሞ
በዲማሚት ተፍልፍሎ፤ ድልድይ ይሁን ሊማ - ሊሞ?

እነዚህ ርእሰ ጉዳዮች በሌሎችም ገጣሚያን ተዳስሰዋል። ዋናው ፍሬ ነገር እና የተመራማሪዎች ጥያቄ መሆን የሚገባው ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድሕንን ገንኖ ያወጣው፤ ከሌሎቹ የሚለየው ከምርታማነቱ ከፈጣንነቱ በተጨማሪ ምንድን ነው የሚለው ይመስለኛል።

**ከህልፈተ ሕይወት ማግስት፡-**

ከብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድሕን ህልፈተ ሕይወት በኋላ አንዳንድ መዘከራዊ እንቅስቃሴዎች ታይተዋል።

**የፀጋዬ ምሽቶች፡-** የመጀመሪያውን ሙት አመት አስመልክቶ የባለቅኔው የፀጋዬ ገብረመድሕን ምሽት ለአራት ሳምንታት (በDecember 2007) በሀገር ፍቅር ትንሿ አዳራሽ በመንፈስ ልጆቹ አበበ ባልቻ፣ ፈቃዱ ተ/ማርያምና ነቢይ መኮንን አስተባባሪነት ተካሂዷል። ከነዚህ ምሽቶች በአንደኛው የተገኘችው የዋርካ ድረ ገጽ ተሳታፊ እይታዋን እንዲህ ትገልጽልናለች። “በሀገር ፍቅር ትንሿ አዳራሽ “የፀጋዬ ገ/መድሕን መዘከሪያ ምሽት” ነበር። ያለፉትን ሶስት ሳምንቶች የመግቢያ ትኬት ለማግኘት ባለመቻል ችግር ማየት አልቻልኩም ነበር። በብር አይደለም የሚገባው በግብዣ ብቻ ነው። በምሽቱ የፀጋዬ ምርጥ ስራዎች ቀርበዋል። ስለሱ ግጥም አጻጻፍም

አስተያየት በነቢዩ ቆንጆ ተደርጎ ተተንትኗል። ደስ ያለኝ ደግሞ ከዚህ በፊት የትም ሚዲያ ላይ ያልቀረበ ፊልም ታይቶ ነበር...ፀጋዬ አሜሪካን ሆኖ የተቀረጸው... ደስ የሚልም የሚያሳዝንም ምሽት ነበር። እኔማ አንዳንዴ ለማልቀስ ሁሉ እፈልግ ነበር። ዝግጅቱ ላይ አበበ ባልቻ ከኦቴሎ ፍቃዱ ተ/ማርያም ደሞ ከቴዎድሮስ ትያትር ቀንጭበው አቅርበው ነበር...ፍቃዱ የቴዎድሮስን የመጨረሻ ንግግር ሲል ለራሴ እስኪገርመኝ ድረስ አፌ አብሮ ያነበንብ ነበር...እንዲህ እንደተቀረጸብኝ አላውቅም ነበር...መጨረሻ ላይ መነባንቡን ሲጨርስ ሰዉ ብድግ ብሎ ጭብጨባውን ማቆም አልተቻለም ነበር።ያኔስ እንባዬን ለማቆም አልታገልኩም።"

**የፀጋዬ ስራዎች ህትመት**:- የፀጋዬ ቤተሰቦች በ1999 «እሳት ወይ አበባ»ን እንደገና አሳትመው ለሕዝብ አቅርበዋል። ጅምርም ነው እንቀጥላለን ብለዋል አሉ። መልካም ሀሳብ ነው ቢቀጥሉበት።

**የፀጋዬ ድረ ገጾች**:-ሁለት የፀጋዬ ድረ ገጾችን ጅምር አይቻለሁ (www.tsegaye.se) እና ደብተራው እናት ድረ ገጽ ውስጥ። ሁለቱም ጅምሮች ናቸው መጠናከር ይገባቸዋል። የመጀመሪያው ድረ ገጽ የኮፒ መብት ችግር ገጥሞኝ ነው ያለ መሰለኝ በጅምር የቀረው፤ እሱም ቢሆን የማይፈታ ችግር አይደለም የቤተሰቡ መልካም ፈቃድ ካለ።

**የፀጋዬ ፌስ ቡክ**:- (http://www.facebook.com/home.php?#/pages/laureate-tsegaye-gebremedhin/) የፀጋዬ 1370 አድናቂዎች የፌስቡኩ አባላት ሆነዋል። አንዳንድ ውይይቶችም ያካሂዳሉ።አንድ ሲያንሸራሽሩ ያየሁት ሃሳብ በስሙ ቤተ መጻህፍት ለማቋቋም ነው። ማለፊያ ሃሳብ ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ ከደራሲያን መካከል በኢትዮጵያ ምድር ሀውልት የቆመላቸው አንድ ብቻ ናቸው «አኖሲሞስ ነሲብ» በትውልድ ቀያቸው። ሀውልት ማቆምም ወይንም ደግሞ እንደበአሉ ግርማ ት/ቤትም በስሙ መሰየምም ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦች ናቸው። የቀድሞው ኢትዮጵያ መጻህፍት ድርጅት (ለበአሉ ግርማ) እና የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም (ለመንግስቱ ለማ) እንዳደረጉት ኤግዝቢሽኖችም ማዘጋጀት ይቻላል።

**የፀጋዬ ሽልማት**:- የፀጋዬ መታሰቢያ ሽልማት በቤተሰቦቹና በወዳጆቹ ትብብር ተቋቁሞ ለሁለት የመጀመሪያ አሸናፊዎች ሽልማት መሰጠቱም ከዚህ በፊት በዜና ተዘግቧል። ይበል የሚያሰኝ ነው።

**የፀጋዬ አመታዊ የቲያትር ፌስቲቫል**:-በኔራን ሠረቀ ብርሃን እና ከአስር በላይ የፀጋዬን ቲያትሮች በማዘጋጀት የሚታወቀው አባተ መኩሪያ እና ሌሎች በጎ ፈቃደኞች በትብብር ይህንን አመታዊ የትያትር ፌስቲቫል ማዘጋጀት ጀምረዋል።

**እንደማሳረጊያ**

ይህች ጽሁፍ ፀጋዬን እንዲህ ዘከራዋለች። ሞቱን ልደቱን ግጥሙን እያነሳሳች። ዘንድሮ የብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድሕን የሞተበት አራተኛ አመት የኢትዮጵያ ደራሲያን ማሕበር የሚከበርበት አምሳኛ አመት ነው። የፀጋዬ ቤተሰቦች ስራዎቹን ሳይደክሙ እንደ 1999 እሳት ወይ አበባ ለሕትመት ቢያቀርቡ፣ የብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድሕን ቀዌሳን ሶስት አስርት የዘለቀ የ«ካባራ አፍሪካ» ጥናት እልባት አስገኝተውለት የህትመት ብርሃን ቢያሰገኙለት፣ ማሕበሩም ስራዎቹን በማስታወስ ቢዘክረው እኛም በአቅማችን የፀጋዬ ፋን ክለብ አባል በመሆን ስራዎቹን ብንዘክር መልካም ነው እላለሁ።

**የብላቴን ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድሕን ነብስ ይማርልን! መንግሥተ ሰማያት ያዋርስልን!**

**ምስጋና**

ሳያሰልሱ ሳይታክቱ የፀጋዬን ስራዎች ለማስተዋወቅ የጣሩትን ቢያንስ የማውቃቸውን የ«**ሸንጎ ኢትዮጵያ**» ዋና አዘጋጅ ተዘራ ፍሬውን፣ ኄራን ሠረቀ ብርሃንን፣ አበበ ባልቻን፣ ነቢይ መኮንንን እና የአንድነት ስነፅሁፍ ክበበ መስራቾች እነ ብሩክ አብዱን፣ በፌስ ቡክ የፀጋዬ ፋን ክበብ አባላትን፣ ለፀጋዬ ድረ ገፅ መስራች፣ ለደብተራው ድረ ገፅ አዘጋጆች፣ ለኢትዮ ፎረምስ ድረ ገፅ መስራች ኦሽን፣ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ የፀጋዬን ስራዎች ሲያስተዋውቁ የነበሩትን አዲስ አድማስ እና ደብተራው ድረ ገጾችን አመሰግናለሁ።

**የፀጋዬ የሚታወቁ ቲያትሮች ያልተጣራ ዝርዝር**

1. King Dionysus and the two brothers
2. በልግ (1957)
3. የደም አክሊል (1958)
4. አስቀያሚ ልጃገረድ (1959)
5. ጆሮ ደግፍ (1959)
6. ሊስትሮ (1960)
7. እኝ ብዬ መጣሁ (1960)
8. ጨሎ (1961)
9. ኮሾ ሲጋራ (1961)
10. የእማማ ዘጠኝ መልክ (1961)
11. ታርትዩፍ (1963)
12. ኦቴሎ (1963)
13. አዝማሪ (1964)
14. ኦዳ ኦክ ኦራክል (1965/ 1967)
15. የከርሞ ሰው (1966)
16. ሀምሌት (1968)
17. ንጉስ ሊር (1968)
18. ማክቤዝ (1968)
19. ክራር ሲከር (1969)
20. ሀ ሁ በስድስት ወር (1974)
21. እናት አለም ጠኑ (1975)
22. አፅም በየገፁ (1975)
23. አቡጊዳ ቀይሶ (1976)
24. ጴጥሮስ ያቺን ሰአት (1976፣ 1994)
25. ኮሊኸገን ኦቭ አልታርስ (1977)
26. መልእክተ ወዛደር (1979)
27. መቅድም (1980)
28. ጋሞ (1981)
29. ዘርአይ ደረስ በሮም አደባባይ (1981)
30. ዚቀኛው አበራ (1986)
31. ሀ ሁ ወይስ ፐ ፑ
32. የፌዝ ዶክተር
33. ቴዎድሮስ
34. የደም አዝመራ
35. ምኒልክ

**ማጣቀሻዎች**

1. አንድምታ የስነጽሁፍ ልሳን ቁጥር 7 መጋቢት-ግንቦት 1999 ኢ.ም።

2. Professor Negussay Ayele. Poet Laureate Tsegaye Gabre-Medhin of Ehiopia: A short walk through his literary park.

3. Ibid.

4.እሸቴ ዘ ጃንሜዳ፤ ወጋየሁ ንጋቱ በአካለ ስንኩል መድረክ:: Downloaded from www.wegayehunegatu.org on December 22/2004.

5. የዮሐንስ ወንጌል፤ መጽሐፍ ቅዱስ 1980. ገጽ 79።

6. አምሃ አስፋው፤ 1995።«ቃል» ይላላ ደነበ ገጽ.44. http://web.missouri.edu/~asfawa/yilala 2002.pdf

7. ነቢይ መኮንን 2000 የእሳት ወይ አበባ ግምገማ። አንድምታ ቁጥር 9 መስከረም-ህዳር 2000 ገጽ 1።

8. http://tezeta.net/49/tribute-to-tsegaye-gabre-medhen. Downloaded on Feb.13,2010.

9. **http://www.ethiopians.com/abay/abay.html**

10. ጉጂ (Penname) አባይ አባይ - የበረሐው ሲሳይ Feb 14, 2004.www.cyberethiopia.com።

11.ነቢይ መኮንን 2006:: ዋ ጋሽ ፀጋዬ! http:// www.addisadmass.com/ Tibeb/ news_item. asp? NewsID=53 (March 18, 2006 issue).

12. ነቢይ መኮንን 2000 የእሳት ወይ አበባ ግምገማ። አንድምታ ቁጥር 9 መስከረም-ህዳር 2000 ገጽ 1።

13. ፀጋዬ ገብረመድሕን:: 1966:: እሳት ወይ አበባ::

14. Ibid.

15. ነቢይ መኮንን 2000 የእሳት ወይ አበባ ግምገማ። አንድምታ ቁጥር 9 መስከረም-ህዳር 2000 ገጽ 11።

16. ፀጋዬ ገብረመድሕን:: 1966:: እሳት ወይ አበባ::

17. ነቢይ መኮንን 2006:: ዋ ጋሽ ፀጋዬ! http:// www.addisadmass.com/ Tibeb/ news_item. asp? NewsID=32 (March 04, 2006 issue).